# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አመሰራረትና ተልዕኮ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዛሬ የተሰጠውን ተልዕኮና የሥራ ድርሻ ይዞ በአዲስ መልክ ከመደራጀቱ በፊት በተለያዩ አወቃቀሮች ውስጥ አልፏል። ተቋሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና አግኝቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በቻርተር የተቋቋመው በ1948 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ ‹‹ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ›› ወይም በእንግሊዝኛ ምህፃሩ (EELPA) በሚል ስያሜ ህጋዊ ሰውነት ይዞ ነበር የተቋቋመው። ይህ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት እስከ 1989 ዓ.ም ሲሠራ ከቆየ በኋላ እንደገና የአወቃቀር ማሻሻያ አድርጎ ‹‹የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን›› (EEPCo) የሚል ስያሜ ተሰጠው ፡፡

ተቋሙ በባለሥልጣንም ይሁን በኮርፖሬሽን አደረጃጀት ሥር በነበረ ጊዜ ከኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ግንባታ ጀምሮ የስርጭትና የአገልግሎት አሰጣጥን በማካተት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። ድርጅቱ ከሚሠራው መጠነ ሰፊ ሥራ አንጻር በአንድ በኩል ተደራሽነቱ እንዳይስተጓጎል ፤ በሌላ በኩል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን በማሳደግ የኢንዱስትሪዎችን ፍላጎት በማሟላት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የተጀመረውን የመንግሥት አቅጣጫ ተከትሎ እንደገና በ2006 ዓ.ም የተለያየ ሚና እና ስያሜ ባላቸው ሁለት ተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP) እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (EEU) በሚል ለሁለት ተከፍሎ ተደራጀ።

በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (EEP) በ2006 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 302/2006 መሰረት ራሱን ችሎ ተቋቋመ። ተቋሙ ከሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 381/2008 እንደገና የተልዕኮ ማሻሻያ ተደርጎበት ሥራውን ቀጠለ።

> ኢትዮጵያ ከተለያዩ አማራጮች ከፍተኛ ኃይል ማመንጨት የሚያስችል ፀጋ ያላት ሀገር ነች። ይህን ኃይል አምርቶ ለሚፈለገው ጥቅም ማዋል ከተቻለ በአጭር ጊዜ የሀገሪቱን ዕድገትና ብልጽግና ማረጋገጥ እንደሚቻል ይታመናል።

በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በዋናነት የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎችን መገንባትና እና የኦፕሬሽን ሥራዎችን ማከናወን፣ ከ132 እስከ 500 ኪሎ ቮልት ያሉ የማስተላለፊያ መስመሮችን መዘርጋት/መገንባትና ማስተዳደር፣ ኃይል እያመረቱ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎችና ለጎረቤት ሀገራት በጅምላ ማቅረብ ዋና ዋና ተግባሮቹ ናቸው። በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 381/2006 አንቀጽ 2 መሰረት ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የተሰጡት ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

1ኛ/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች ፣ ከ66 ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ ማስተላለፊ መስመሮችና ማከፋፋያ ጣቢያዎች የግንባታ ሥራዎች የአዋጭነት ጥናት፣ የንድፍና የቅየሳ ሥራዎች ማከናወን እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በኮንሰልታንት ማሠራት፤

2ኛ/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች ከ66 ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ ማስተላለፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች የግንባታና የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በሥራ ተቋራጭ ማሠራት ፤

3ኛ/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጪያ ጣቢያዎችን ፣ ከ66 ኪሎ ቮልት ኃይል በላይ የመሸከም አቅም ያላቸውን የኤሌክትሪክ ማስተላለፊ መስመሮችን እና ማከፋፋያ ጣቢያዎችን ማስተዳደር ፣ የኦፕሬሽን እና የጥገና ሥራዎችን ማከናወን፤

4ኛ/ ከ66 ኪሎ ቮልት ደረጃ በላይ በሆኑ መስመሮች የኤሌክትሪክ ኃይልን በጅምላ መሸጥና መግዛት፤

5ኛ/ ከ66 ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ሊዝ ማድረግ፤

6ኛ/ የሚሸጠውን የኤሌክትሪክ ኃይል በተመለከተ የታሪፍ ማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

7ኛ/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከሀገር ውስጥ ፣ ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

8ኛ/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ የሚሉት ናቸው።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ያመረተውን ኃይል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል ከማድረግ ባሻገር ለሱዳን፣ ለጅቡቲና ኬኒያ ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሪ በማስገባት ላይ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ከተለያዩ አማራጮች ከፍተኛ ኃይል ማመንጨት የሚያስችል ፀጋ ያላት ሀገር ነች። ይህን ኃይል አምርቶ ለሚፈለገው ጥቅም ማዋል ከተቻለ በአጭር ጊዜ የሀገሪቱን ዕድገትና ብልጽግና ማረጋገጥ እንደሚቻል ይታመናል። በተለይም ግብርናውን ከኢንዱስተሪው ጋር አመጋግቦ በመጓዝ ዘላቂና አስተማማኝ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ከማገዝ አንጻር የኃይል አቅርቦት ሚና የማይተካ ነው።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዘላቂና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል መሰረተ ልማት በመገንባት እና በማስተዳዳር የተመረተውን ኃይል በጅምላ በመሸጥ ወይም በመግዛት ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያስፈልገውን ኃይል የማቅረብ ተልዕኮውን ለማሳካት ተግቶ እየሠራ ያለና በርካታ ስኬቶችንም ያስመዘገበ ተቋም ነው።

አንዳንድ ጊዜ ከመረጃ እጥረት የተነሳ ሰዎች ወይም ተገልጋዮች የኤሌክትሪክ ኃይልና የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ሚና በመደበላለቅ ወይም የአንዱን ሥራ ለሌላው በመስጠት ተቋሙ የማይመለከተውን ጉዳይ የእርሱ የሥራ ኃላፊነት በማስመሰል ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ሲያቀርቡ ይስተዋላል። ይህ ጽf ከፍ በተወሰነ መልኩ ለደንበኞች መረጃ በመስጠት እንዲህ ያለውን ብዥታ ያጠራል የሚል እምነት አለን። ቸር እንሰንብት።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ